# <u>ስለ ኢ.ህአፓ ለመመስከር የግድ ውስጥ አዋቂ መሆን አያስፈልግም!!</u>

ከዘነበ በቀለ

የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግል በግልቡ ላየው ሰው ኢ.ህአፓን መኮነን መክሰስ መወንጀልን እንደፋሽን ሊይዘው ይችላል። ሀቁ ግን ኢ.ህአፓ የትግል መማሪያ ድርሳን መሆኑን ከመረዳቱ ላይ ነው። በየወቅቱ በሚፈጠሩ ግርግሮች ሳይቦርቅ በሚደርስበት አደጋ ሳይደናገጥ ለዘለቄታው በማለም የህዝብን የበላይነት ለማምጣት ቀጣይነት ያለው ትግል የሚያካሂድ ድርጅት መሆኑን ከመቀበሉ ላይ ነው ሀቁ። በግሌ እንደ ኢ.ህአፓ የሩቅ ተመልካች በጠላትነት ባልሰለፍም በድሉ መራዘም ሳቢያ ሳልወቅሰው ቀርቼ አላውቅም። የተረዳሁት ነገር ቢኖር ግን በዛሬ ጧት የሆይሆይታ ትግል የዛሬ ማታን ድል አልሞ የሄደ ድርጅት አለመሆኑን ነው። ባለመሆኑም የፖለቲካውን ውጣ ውረድ ገና ከጅምሩ ያወቀና የተረዳ ድርጅት ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ታጋዮቹ በሙሉ በልጅነት ዕድሜያቸው ተረማምደው በጎልማሳነት ዘመናቸው የትግል ፍሬአቸውን ባለማየታቸው ተስፋ የቆረጡና ትግልን የሸሹ አለመሆናቸው ሌላው ትልቁ የኢ.ህአፓ ሃያልነት መገለጫ ነው እላለሁ።

የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት መጠበቅ ውስጣዊ መደላድሎችን ማስተካከል፣ ኢትዮጵያን በልማት አሳድጎ ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ ጋር በዕኩልነት ደረጃ እንድትታይ ማድረግ፣ ሲቻልም የቀድሞ ገናና ስሟን ማረጋገጥ ዓላማው መሆኑን ኢ.ህአፓ በተግባሩ አሳይቷል። ህዝብን ያለምንም አድልዎ በዕኩልነት ለማስተዳደር፡ የሚያስችል ህብረተሰባዊ ስርዐትን መገንባት አማራጭ አድርጎ በመንቀሳቀሱ ካስመሳዮች ሁሉ ጋር ተጋጭቷል። ህዝባዊ መንግስትን በመጠየቁ ተነቅፏል። ዲሞክራሲ ያለገደብ ብሎ በመታገሉ ተወግዟል። የብሄረሰቦች ዕኩልነትን አጎልቶ በማሳየት ህዝብን በመቀስቀሱ ተወንጅሏል። ምንም እንኳ ለብሄረሰቦች እኩልነት የቆመበት መንገድ ሚልጠ የጠባቦች መንሸራተቻ ለመሆን ቢዳዳውም፣ ጠባብ ብሄረተኝነት ስሜት መንገዱ ባፍጢም የሚደፋ አሳሳች መሆኑን ለተራማጅ ሁሉ አስጠንቅቋል። ባንፃሩም የባህል የቋንቋ እኩልነትን ሰብኳል። ወጣቱ ከራስ ጥቅም በላይ ሀገርና ህዝብን ማስቀደም እንደሚገባው አስተምሯል። በሀገሩ ጉዳይ ላይ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ኮንኗል። በድርጊቱም ከጠባቦች ተዋግቷል። ከተገንጣዮች ተሟግቷል። መሪዎቹን አባላቱን ለሞት ለስቃይ አበርክቷል። ለስደት ዳርጓል፣ ተንገላቷል። ግን ትግሉን አላቆመም።

ድልን በአንድ ሌሊት ጀምበር ለማየት ቅዠት ውስጥ ያልገባ ድርጅት ለመሆኑ እስካሁን ድረስ ከትግል መድረክ ያለማፈግፈጉ ምስክር ይሆናል። ረዥምና ቀራጥ ትግል የሚያስፈልገው መሆኑን አምኖ ነውና የሚንቀሳቀሰው፣ በግለሰቦች የመንፈስ ድካም፣ በግለሰቦች ክዳት አይሸበርም። ሁል ጊዜ ተጓዥ ነው። ሁልጊዜ ወደ ድል ጎዳና አቅኚ ነው። ለዚህ ብዙ ማስረጃ ማቅረብ የሚያስፈልገው አይመስለኝም። ምክንያቱ በታለፉት የትግል ዘመናት በሙሉ፣ ዓላማውንም ሆነ የትግል ፅናቱን እንደያዘ መዝለቁ ታይቷልና። ኢ.ህአፓ እንደገጠመው ችግር ቢሆን ኖሮ በአሁኑ ወቅት በትግል አለም ውስጥ ባልታየ ነበር። በርካታ ድርጅቶች የውሃ ሽታ ሆነው በቀረቡት በአሁኑ ወቅት የህዝቡን የትግል መንፈስ እያነቃቃ፣ አይዞህ

በርታ! እያለ፣ የትግል ፅናቱን እንዲያድስ እየመከረ፣ በትግል አርያነት የሚኳዘው ኢ.ህአፓ ለመሆኑ ዋቢ መጥራት አያስገልግም።

ኢ.ህአፓ ሲታገሉት የሚያሸት፣ ሲረበርቡት የሚያፈራ መሆኑን በማስመስከር አብረውት የነበሩ ድርጅቶች በሙሉ ሲከስሙ፣ በብቸኝነት ነጥሮ በመውጣት የትግል አማራጭ ሆኖ ለአራት አስርተ ዓመታት ዘልቋል። የዘለቀው እንዲሁ በከንቱ አይደለም፣ በአመራር ብቃቱ እንጂ!። ኢ.ህአፓ ወቅታቸውን እየጠበቁ እንደተንጠባጠቡት ድርጅቶች አልጠፉም፣ መሬት ለመሬት፣ ውስጥ ለውስጥ ተጉዞ “ እዚህ ሲሉት እዚያ!-እዚያ ሲሉት እዚህ!” እያለ፣ ለጠላቶቹ ሳይመች እስካሁን የዘለቀ ድርጅት መሆኑ አኩሪ ገድሉ ነው። የተከተለው መስመር ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ፣ የዓላማ ውኸ'ንብርን ያስወገደ፣ ጊዜያዊ ድልን ሊያስገኝ የሚችልን መንገድ ያልተከተለ፣ በዘለቂው ድል ላይ ያማተረ፣ በጥቅማጥቅም የማይሸመደመድ መሆኑ ተደጋግሞ ተረጋግጧል። ያ! ችሎታ ባይኖረው ኖሮ የውስጥ ጠላቱ ቀርቶ የውጭ ጠላቶቹ እስካሁን ባጠፉት ነበር። ሌሎች ይህን ውጣ ውረድ መዝለቅ ያቃታቸው ድርጅቶች ተመሳሳይ የአመራር ብቃት በማጣታቸው እንጂ! ደጋፊዎቻቸው በስራቸው ተሰልፈው ሲንቀሳቀሱ የትግል ፍላጎት፣ የሀገር ፍቅር ስሜት ያጡ በመሆናቸው አይደለም።

አንድ ድርጅት የጠራ አቅዋም ይዞ መነሳት ምንም ጊዜ ቢሆን ይጠበቅበታል። የተልፈሰፈሰ መሪ ተከታዮቹን እንደ ፈረስ ግልቢያ ለፍርጠጣ ውድድር ይጋብዛል። የኢ.ህአፓ ታጋዮች፣ ደጋፊዎች የተለዩ ሆነው ሳይሆን፣ አላማ ያለው የድርጅት አመራር፣ ተክለሰብነትን ያስወገደ የጋራ አመራር ስላላቸው፣ ግንባራቸውን ለጥይት ሰጥተው “ኢ.ህአፓ ያቸንፋል” እያሉ በኩራት የተሰዉ ለመሆናቸው በዚያ ህይወት ያለፈ ሁሉ የዐይን ምስክር ነው። በህይወት ያሉ አባላቱ እስከዛሬ ድረስ በፅናት ሊዘልቁ የቻሉት። በርካቶች ህይወታቸውን ለመስጠት የበቁት በዚሁ እምነታቸው ነው። ህይወትን ሊሰጥ የሚችል ካድሬ ማፍራት፣ ብትነግድ ያልፍልሃል። አፍህን ዘግተህ ብትቀመጥ አደጋ አያገኝህም። ጥገኛ ሆነህ ብትኖር በሀብት ትከብራለህ። እያሉ እንደመሰበክ አይቀልም። ዓላማን ማሳመን የግድ ይላል። የሰው ልጅ ለወገኑ ሲል ህይወቱን ለመስጠት የሚያሰችለው ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ የሆነ የላቀ የአስተሳሰብ እርከን ላይ መገኘትን ይጠይቃል።

ለእኔ በእጅጉ የሚያስደንቀኝ ኢ.ህአፓ ምንም እንኳ ተደጋጋሚ ክዳት ቢገጥመውም፣ ችግሩ ድርጅቱን ሊያንኮታኩት የሚያስችል ሆኖ አለመገኘቱ ነው። ይህ የሆነው ለሁሉም ጥቃቶች በር የከፈተ ባለመሆኑና ጠንቃቃ አመራር በመኖሩ ይመስለኛል። ዓላማን ከቅርብ ጊዜ ድል ጋር የሚያገናኙ አባላት በተስፋ ቆራጭነት እራሳቸውን ከማግለል ውጭ ያደረሱት አደጋ በውል አይስተዋልም። ያ! ብቻ ሳይሆን በክዳት የተሰለፉት በሙሉ አማራጫቸው ከጠላት ካምፕ ውስጥ መግባት መሆኑ፣ የጠላት መናጆ ሆነው ለውርደት መዳረጋቸው፣ በነ ታምራት ላይኔና መሰሎቹ ላይ ተስተውሏል። ኢ.ህአፓን አጥፍተን ወይም በሌላ ተክተን እንጓዛለን ብለው የተነሱት ዛሬ ምርጫቸው ለእንባ ማበሻ መሃረብ ገበያ መዋል ሆኗል። በክብር የጀመሩትን የጀግንነት ህዝባዊ ትግል በመክዳታቸው፣ በቅጣትና በውርደት እጅ ሰቅሎ አምላክን እያለቀሱ እስከመለመን ያደረሳቸው መሆኑ ታይቷል። ዓላማ

ቢስን፤ ከዳተኛን፤ አምላክም አያምነውና፤ ድርጊታቸው አሁንም የእንቧይ ካብ ከመሆን አያልፍም።

ሀቅን ይዞ መራመድ የጊዜ ገደብ የሌለው መሆኑን፡ ቆራጥ እና ፅኑዕ አቅዋም መያዝ በትግል አስፈላጊ መሆኑን፡ ለቀጣዩ ታጋይ ትውልድ ሁሉ ያስተማረው ኢህአፓ ነው ቢባል ሀሰት አይሆንም። አሁንም የትግል ፅናትን እያስተማረ ያለው ይኸው ድርጅት ነው። ትግል በልጅነት ዕድሜ ተጀምሮ ባፍላነት የሚጠናቀቅ ለሚመስላቸው፤ ረዥምና አሰልቺ ውጣ ውረዶች ያሉበት መሆኑን ላላወቁ፤ ቆንጠጥ ብላችሁ ግቡበት ብሎ የሚመክር ድርጅት ኢህአፓ ብቻ ነው። ትናንት ያዙኝ ልቀቁኝ፤ ዛሬ ደብቁኝ የሚል ታጋይ ያፈራ ድርጅት ሁሉ በስራው እንዲያፍር ያደረገው ኢህአፓ ነው። ዛሬም እንደትናንቱ ለሀቅ ለእውነት በፅናት መቆም የማንኛውም ታጋይ ግዴታ ነው ብሎ የሚያስተምረው ኢህአፓ ነው። እናም ትናንትም ሆነ ዛሬ በእምነቱ ፀንቶ፤ በአመነበት ኮርቶ የሚናገር አባል ማፍራት ከፍተኛ ጥበብን ይጠይቃል። በአሁኑ ሰዓት ለወያኔ የቀን ቅዠት የሆነበት ኢህአፓ የዚህ ሁሉ ጥበብ ባለቤት መሆኑን የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም።

ሀገር ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ የተፈረደበት ኢህአፓ በሀገር ውስጥ ለመቆየት በህዝብ መሃል ለመገኘት ከወያኔም ሆነ ከአባሪዎቹ ባዕዳን ፍቃድ አልጠየቀም። መጠየቅም አይገባው። የሀገሪቱ ጠላቶች የህዝቡ አሰቃዮች የኢህፓን በህዝብ መሃል መንቀሳቀስ አጥብቀው የሚጠሉበት ምክንያት አላቸው። ምክንያቱም ወያኔም ሆነ አባሪዎቹ በሀቅ ሊገጥሙት አይቻላቸውምና ነው። ህዝብን ለመቅረብ ኢህአፓ ያለውን ሀይል ያውቁታልና ነው። ወያኔም ሆነ የባዕዳን አጫፋሪዎቹ ያልተረዱት፤ ምናልባትም ዘግይተው ያወቁት ነገር ቢኖር፤ በር ዘግቶ መሰንበት ያለመቻሉን ነው። ልክ በረከት ስምኦን የምርጫ ካርዱን የቀማን ነፋስ እንዳለው አይነት መግጠሙ አይቀሬ ነውና። ኢህአፓ ከምንም ውስጥ ለመግባት በር የማያግደው መሆኑ ተደጋግሞ ተመስክሯል። ኢህአፓ ጠላቶቹ ነን ከሚሉ ጋር ሁሉ ቀርቦ በምክንያት ለመከራከርም ሆነ በጥሞና ለመነጋገር ዕድል ካገኘ በደቂቃ ውስጥ አስተሳሰብን የማስለወጥ ክህሎት ያለው ድርጅት መሆኑ ታይቷል። ይህን ዕድል እነፍግሃለሁ ከተባለም በጠላቱ ጉልበት ተተክሎ እንደሚለመልም ዕፅዋት ከመሃል መቀመጥ እንደማያዳግተው ደጋግሞ አስመስክሯል።

ኢህአፓ ሀገሪቱ ካፈራቻቸው ምሁራን መሃል በአብዛኛው የተደገፈ ድርጅት ነበር። አሁንም ነው። ከማንኛውም ድርጅት በላይ አባሎቹን በጥቅም ሳይሆን በዓላማ አሳምኖና አሰልፎ ያታገለና፤ የሚያታግል ብቃት ያለው ድርጅት ነው። ከማንም ድርጅት በላይ አመራሩ የኢትዮጵያን ሁኔታና የዓለምን ሁኔታ አገናዝቦ መራመድ የሚችል ለመሆኑ የዛሬው ህልውናው ይመሰክራል። አለበለዚያ ድርጅቱ በበርካታ የህዝብ ጠላቶች መሃል አልፎ ለመቆየቱ እግዜር ይጠብቀዋል ብሎ መደምደም ነው አማራጭ የሚሆነው።

በእውነቱ! ስለ ኢህአፓ ለመመስከር ኢህአፓ መሆን አያስፈልግም። የሚያስፈልገው ተገቢውን ስፍራ ለሀቅ ሰጥቶ እውነትን ለመናገር መድፈር ብቻ ነው። አንዳንድ ሰዎች እስከዛሬ ደረስ የዘለቀ ቂም ቋጥረው ሰለሚጓዙ፤ በደርግም ሆነ በወያኔ ውስጥ ገብቶ ህዝብ ሲያሰቃይ የነበረ ሰውን መቅረብ ይቀላቸዋል።

በደርግም ሆነ በወያኔ ባለስልጣናት ላይ አንዲት ቃል ከመናገር በኢ.ህአፓ ላይ የሀሰት ወንጀል መደርደርን ይመርጣሉ። ኢ.ህአፓ ስልጣን ይዞ ሲያስተዳድር ህዝብ በደለ ብሎ መናገር የሚችል አይገኝም። ሲያታግል ተሳሳተ ማለትና ወንጀለኛ ነው ማለት የተለያየ ነገር ነው። ያም ቢሆን ግን የትግልን ምንነት መረዳትን ይጠይቃል። ስልጣን ይዘው በስልጣናቸው ህዝብን ካጎሳቆሉ እኩል፣ ኢ.ህአፓን በአፍራሽ መልኩ መፈረጅ የሚችል ጭንቅላት የዛሬውን የሀገሪቱን የፖለቲካ አቅጣጫ የተገነዘበ ነው ለማለት አያስደፍርም። በትናትናውም ቢሆን ከሀቅ ጋር ያጋጨዋል። ዛሬ ወያኔን መታገል የሚችሉ ቁርጠኛና ጥበበኛ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ ድርጅቶች ያስፈልጋሉ። ከቁርጠኝነትና ከጥበበኝነት ያፈነገጠ ታጋይ ዞሮ ዞሮ ማረፊያው ከወያኔ እጅ ከመሆን አያልፍም። ስለዚህም ኢ.ህአፓን የምንሳሳለት በትግሉ የምናከብረው እንጂ! የምናናንቀውና የምንጠላው መሆን እንደማይገባ ማወቅ ለሀገርም ለህዝብም ይጠቅማል እላለሁ። ለሀገርና ለህዝብ የሚያስብ ሁሉ ኢ.ህአፓንና፣ መኢአድን በስስት ዓይኑ መመልከት ይገባዋል።

//////////